Week 30

Grade 1

# መናናቅ



Read Aloud

# መናናቅ

Read Aloud | Grade 1 | Week 30



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ባልና ሚስቱ የእደጥበብ ባለሙያዎች ናቸው።



ሁልጊዜ ባልና ሚስቱ
የእኔ ስራ ይበልጣል፣
በማለት ይናናቃሉ።

አንድ ቀን “ለአንድ ሳምንት ስራ እንቀያየርና የትኛው እንደሚበልጥ እንመልከት” በሚል ተስማሙ::



ሚስት በአንድ ሳምንት
ሁለት ጋቢ ብቻ ሰራች።



ባል ደግሞ አንድ ጀበና ብቻ ሰራ:: ጀበናውም ሰንጣቃና ጠማማ ሆነበት::



በሳምንቱ መጨረሻ
የስራቸውን ውጤት አዩ።



ችግሩ የስራው አይነት ሳይሆን የሙያ ልምድ እጥረት እንደሆነ ተረዱ።



“ከበሮ በሰው እጅ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር” በማለት ተረቱ።



የሁለቱም ስራ ክቡርና ሙያ የሚጠይቅ መሆኑን አመኑ፡፡

ከዚያ ቀን ጀምሮ ልምድ ተለዋወጡ፡፡

ሁለቱንም ስራዎች እየተጋገዙ ሰሩ። በጣም ሀብታም ሆኑ።

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ።

1. ባልና ሚስቱ የተናናቁት ለምንድን ነው?
2. ባልና ሚስቱ በመናናቃቸው ምን ችግር ገጠማቸው?